**የSEA (የሲያትል የትምህርት ማኅበር) የ2026 የድርድር ፍላጎቶች**
**ማርች 31፣ 2026**

## ካሳ እና ጥቅማጥቅሞች

- ከፍተኛ ብቃት ያላቸውን አስተማሪዎች የሚስብ እና ስራቸው ላይ እንዲቆዩ የሚያደርድ፣ ከአካባቢው ወረዳዎች ጋር ተወዳዳሪ የሆነ፣ እንዲሁም በትልቁ የSeattle ሜትሮፖሊታን አካባቢ ያለውን የኑሮ ውድነት ግምት ውስጥ የሚያስገባ ካሳ መክፈል። ከተጨማሪ የሥራ ሰዓት፣ ኃላፊነት፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ከሚከናወኑ ተግባራት እና ከሌሎች ተጨማሪ ኃላፊነቶች ጋር በተያያዘ ተገቢውን የማካካሻ ክፍያ መክፈል።

- ከፍተኛ ብቃት ያላቸውን አስተማሪዎች ለመመልመልና ለማቆየት እንዲያግዝ፣ ለሁሉም ብቁ ሠራተኞች በተቻለ ፍጥነት ተመጣጣኝና ጥራት ያለው የጤና መድን ተደራሽ ማድረግ።

## ውጤታማ የማስተማር እና የመማር ሥርዓት፣ የተማሪዎች ድጋፍ እና የወረዳው የአሠራር ሂደቶች

- የተማሪዎችን የመማር ብቃት እና ማህበራዊ-ስሜታዊ እድገት የሚያጎለብቱ፣ ጠቃሚ፣ አሳታፊ እና ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲሰጡ አስተማሪዎችን የሚያግዙ የጋራ ድርድር ስምምነቶች ማጽደቅ።

- ውጤታማ መማር ማስተማርን የሚያበረታታ፣ እንዲሁም አስተማሪዎች የተማሪዎችን የዕውቀት እና ማህበራዊ-ስሜታዊ ፍላጎቶች በእኩል ደረጃ ለማሟላት የሚያስችሉ ግብዓቶችን የሚያቀርብ ምቹ የመማሪያ ቦታ መፍጠር ።

- የግብዓት አመዳደብን፣ የደህንነትና የምላሽ ዕቅዶችን እንዲሁም የሙያ ክህሎት ማሳደጊያ ሥልጠናዎችን ለመቅረጽ በሚደረግ ውሳኔ ላይ በትምህርት ቤት እና በፕሮግራም ደረጃ የሠራተኞች ተሳትፎን ማረጋገጥ።

- ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት እና አገልግሎት አሰጣጥን ለማረጋገጥ፤ ለግል እና ለጋራ ዕቅድ፣ ዝግጅት፣ ምዘና እንዲሁም ለሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች በቂ ጊዜን መመደብ።

- ተገቢነት ያለው፣ የተቀናጀ፣ ክህሎትን የሚያጎለብት፣ ዕውቀትን የሚገነባ እና ውጤታማ አሰራርን የሚያበረታታ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና መስጠት።

- አዎንታዊ የተማሪ ውጤቶችን የሚያስገኝ፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ትምህርት እና አገልግሎቶችን ማቅረብ። የትምህርት ቤት ማህበረሰባችንን ልዩነት የሚያንፀባርቁ ሠራተኞችን መመልመል እና በሥራ ላይ እንዲቆዩ ማድረግ።

- ለተማሪዎችና ለወረዳው የአሠራር ሂደቶች ስኬታማነት አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ተግባራትን ለመወጣት የሚያስችሉ፣ በቂ ግብዓቶች የተሟሉላቸው ምቹ የሥራ ቦታዎች መፍጠር።

**የልዩ ትምህርት ድጋፍ እና አገልግሎት አሰጣጥ**

- ለልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች የተማሪዎችን ፍላጎት በወቅቱ በመለየትና በመመዘን፤ ፍላጎታቸውን የሚያሟሉ ወጥ እና ወቅታዊ ምላሽ ሰጪ አገልግሎቶችን ማረጋገጥ።

- ሁሉን አቀፍ እና አሳታፊ የትምህርት ሥርዓትን መሠረት በማድረግ፤ የተማሪዎችንና የሠራተኞችን ደህንነት የሚያስጠብቁ፣ እንዲሁም ተማሪዎች የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የሚያግዙ የተቀናጁ መዋቅሮችና የአሠራር ሂደቶች መኖር።

- በደንብ በሰለጠኑ የSEA አስተማሪዎች አማካኝነት ጥራት ያለው መረጃ መሰብሰብ እና የተሻሻለ የትምህርት ሥርዓተ ማቅረብ።

- የትምህርት ሥርዓቱን ለማዘጋጀትና ለማሻሻል፣ IEP (አይ ኢ ፒ) ለመጻፍ፣ እንዲሁም ከሕግ ጋር የሚስማማ እና ሁሉንም ባሳተፈ የትምህርት ሞዴል ውስጥ ትብብርን የሚያመቻች Specially Designed Instruction (SDI፣ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ ትምህርት) ለመፍጠር የሚያስችል ጊዜ መመደብ።

**በሥራ ቦታ ሊኖሩ የሚገቡ ዋና ዋና መብቶች**

- የፍትሃዊ የሕግ ሂደት መብቶችን (Due Process Rights) ተከታታይነት ባለው፣ ፍትሃዊ እና እኩል በሆነ መንገድ መተግበር፣እንዲሁም SEA የውክልና ኃላፊነቱን እንዲወጣ፣ አለመግባባቶችን በወቅቱ እንዲፈታ እና ግጭቶችን እንዲቀንስ የሚያስችል መረጃን በወቅቱ ይፋ ማድረግ።

- ደኅንነቱ የተረጋገጠ፣ ልዩነትን የሚደግፍ እና ፍትሃዊነትን የሚያከብር የመማር ማስተማር ሁኔታዎችን መፍጠር። ሕገ-ወጥ እና ተገቢ ባልሆኑ የመንግስት አሰራሮች የተጎዱ ሠራተኞችን ሰብዓዊ መብቶች እና የሥራ ዋስትና መጠበቅ።

- የጋራ መግባባትን የሚያመቻች እና ግጭትን የሚቀንስ፣ ግልጽ እና ተደራሽ የሆነ የውል ቋንቋን መጠቀም።

---